የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETTE

**OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**

ሃያ ሦስተኛ ዓመት ቁጥር ፸፬
አዲስ አበባ ነሐሴ ፩ ቀን ፪ሺ፱ ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

23rd Year No 74
ADDIS ABABA, 7th August 2017.

## ማውጫ

አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፵፱/፪ሺ፱ ዓ.ም
የወሳኝ ኩነት ምዝገባ እና የብሔራዊ መታወቂያ (ማሻሻያ) አዋጅ.......... ፱ሺ፰፻፲፩

## CONTENT

Proclamation no.1049/2017
Vital Events Registration and National Identity Card proclamation (amendment) proclamation…………….9811

## አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፵፱/፪ሺ፱

## የወሳኝ ኩነት ምዝገባና የብሔራዊ መታወቂያ አዋጅን ለማሻሻል የወጣ አዋጅ

የወሳኝ ኩነት ምዝገባ ከተጀመረ በኃላ ከአገልግሎት አሰጣጡ ጋር በተያያዘ ያጋጠሙትን የአሰራር ክፍተቶች ለመቅረፍ እና አገልግሎቱን የተሟላ ለማድረግ የወሳኝ ኩነት ምዝገባ እና የብሔራዊ መታወቂያ አዋጅ ቁጥር ፯፻፷/፪ሺ፬ን ማሻሻል አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ-መንግስት አንቀጽ ፶፭(፩) መሰረት የሚከተለው ታውጇል;-

### ፩. አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ "የወሳኝ ኩነት ምዝገባ እና የብሔራዊ መታወቂያ (ማሻሻያ) አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፵፱/፪ሺ፱" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

### ፪. ማሻሻያ

የወሳኝ ኩነት ምዝገባ እና የብሔራዊ መታወቂያ አዋጅ ቁጥር ፯፻፷/፪ሺ፬ እንደሚከተለዉ ተሻሽሏል፤

፩/ የአዋጁ አንቀጽ ፪ ንዑስ አንቀጽ (፰) ተሰርዞ በሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀጽ (፰) ተተክቷል፤

## PROCLAMATION No.1049/2017

## A PROCLAMATION TO PROVIDE FOR THE AMENDMENT OF THE VITAL EVENTS REGISTRATION AND NATIONAL ID PROCLAMATION

**WHEREAS** it has become necessary to amend Vital Events Registration and National ID Proclamation No. 760/2012 to avoid service delivery gaps identified during vital event registration and in order to make the service comprehensive.

**NOW, THEREFORE,** in accordance with Article 55 (1) of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia, it is hereby proclaimed as follows;-

### 1. Short Title

This Proclamation may be cited as the "Vital Events Registration and National Identity Card proclamation (amendment) Proclamation No 1049/2017".

### 2. Amendment

The Vital Events Registration and National Identity Card Proclamation No.760/2012 is hereby amended as follows:

1/ Sub-article (8) of Article 2 of the Proclamation is deleted and is replaced by the following new sub-article (8):



www.chilot.me

“፰/ ‘የአስተዳደር ጽሕፈት ቤት’ ማለት የወሳኝ ኩነት ምዝገባ የሚከናወንበት የክልል ዝቅተኛው የአስተዳደር እርከን ወይም የወሳኝ ኩነት ምዝገባ መዋቅር ነው፤”

፪/ የአዋጁ አንቀጽ ፫ ንዑስ አንቀጽ (፩) ተሰረዞ በሚከተለዉ አዲስ ንዑስ አንቀጽ (፩) ተተክቷል፤

“፩/ የወሳኝ ኩነት ምዝገባን በሚመለከት በማንኛዉም ኢትዮጵያዊ ወይም በኢትዮጵያ ውስጥ በሚገኙ የውጭ ዜጎች፤” እና

፫/ ከአዋጁ አንቀጽ ፮ ንዑስ አንቀጽ (፪) ቀጥሎ የሚከተለዉ አዲስ ንዑስ አንቀጽ (፫) ተጨምሯል፤

“፫/ በኢትዮጵያ ሚሲዮን፣ በብሔራዊ መረጃ እና ደህንነት አገልግሎት፣ በኢትዮጵያ መርከቦች እና በሀገር መከላከያ ሚኒስቴር እንደ ክብር መዝገብ ሹም ሆነዉ እንዲያገለግሉ የተመደቡ አካላት እንደ አግባብነቱ ለክልል ክብር መዝገብ ሹሞች የተሰጡ ተግባራት እና ኃላፊነቶች ይኖራቸዋል፡፡”

፬/ የአዋጁ አንቀጽ ፯ ተሰረዞ በሚከተለዉ አዲስ አንቀጽ ፯ ተተክቷል፤

“፯. **<u>የኢትዮጵያ ሚሲዮን እና ስለስደተኞች</u>**

፩/ የኢትዮጵያ ሚሲዮን በዉጭ ሀገር ለሚኖሩ ኢትዮጵያዊያን እንደ አስተዳደር ጽሕፈት ቤት ሆነዉ ያገለግላሉ፤ ሚሲዮኑ እንደ ክብር መዝገብ ሹም ሆኖ የሚሰራ ሰራተኛም ይመድባል፤ በሚሲዮኑ የሚመደብ ሰራተኛ እንደክብር መዝገብ ሹም በመሆን ይሰራል፡፡

፪/ ሚሲዮን በሌለበት ሀገር የሚኖሩ ኢትዮጵያዊያንን የሚመለከቱ ወሳኝ ኩነት ምዝገባ የዉጭ ጉዳይ ሚኒስቴር በሚያወጣዉ መመሪያ መሰረት የሚፈጸም ይሆናል፡፡

፫/ የብሔራዊ መረጃ እና ደህንነት አገልግሎት ስደተኞችን በሚመለከት እንደ አስተዳደር ጽሕፈት ቤት ሆኖ ያገለግላል፤ እንደ ክብር መዝገብ ሹም ሆኖ የሚሰራ ሰራተኛም ይመድባል፡፡”

“8/ ‘Administrative office’ means an office of a regions lowest level of administrative hierarchy or vital event registration structure;

2/ Sub-article (1) of Article 3 of the Proclamation is deleted and is replaced by the following new sub-article (1):

“1/ to any Ethiopian or foreigners found in Ethiopia with respect to the registration of vital events;” And

3/ The following new sub-article (3) is added after sub-article (2) of Article 6 of the Proclamation:

“3/ The bodies assigned as a civil status by the Ethiopian Mission, the National Intelligence and Security Service, the Ethiopian Ship and the Ministry of National Defense, as appropriate, shall have duties and responsibilities of civil status of regions.”

4/ Article 7 of the Proclamation is deleted and replaced by the following new Article 7:

**“7. <u>Ethiopian Mission and Refugees</u>**

1/ The Ethiopian Missions shall serve as administrative office for Ethiopians residing in foreign countries; and the staff assigned by the Ethiopian Mission shall act as an officer of civil status.

2/ Registration of vital events with respect to Ethiopians residing in a country where there is no Ethiopian Mission shall be carried out in accordance with directive to be issued by the Ministry of Foreign Affairs.

3/ The National Intelligence and Security service shall serve as administrative office for Refugees; and shall assign staff to act as an officer of civil status.

www.chilot.me

፭/ የአዋጁ አንቀጽ ፲፩ ንዑስ አንቀጽ (፩) ተሰርዞ በሚከተለዉ አዲስ ንዑስ አንቀጽ (፩) ተተክቷል፤

"፩/ ማንኛዉም የክብር መዝገብ በጥራዝ መልክ ወይም አግባብ ባለው ቴክኖሎጂ ሥርዓት ተዘጋጅቶ ይደራጃል፡፡"

፮/ የአዋጁ አንቀጽ ፳፫ ተሰርዞ በሚከተለዉ አዲስ አንቀጽ ፳፫ ተተክቷል፤

**፳፫. ስለፊርማ**

በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፳፪ መሰረት በክብር መዝገብ የሰፈሩ መረጃዎችን በፊርማ ማረጋገጥ ያለበት ሰው፣

፩/ ፊርማው በጽሑፍ መፈረም አለበት፤

፪/ በጽሁፍ መፈረም የማይችል ሰው በጣት አሻራው ይፈርማል፤

፫/ በጽሁፍ ወይም በጣት አሻራ መፈረም የማይችል ከሆነ ያልቻለበት ምክንያት ተገልፆ ምስክር ባለበት ክብር መዝገብ ሹሙ ይፈርማል፡፡

፯/ የአዋጁ አንቀጽ ፳፬ ንዑስ አንቀጽ (፪) ተሰርዞ በሚከተለዉ አዲስ ንዑስ አንቀጽ (፪) ተተክቷል፤

"፪/ የሕፃኑ ወላጆች ሙሉ ስም፣ የትውልድ ቀን እና ቦታ፣ መደበኛ መኖሪያ ቦታ፣ የጋብቻ ሁኔታ፣ ዜግነት፣ ሀይማኖት፣ ብሔር እና የወላጆቹ ወይም የተወከለዉ ወላጅ ፊርማ፤"

፰/ የአዋጁ አንቀጽ ፳፰ ንዑስ አንቀጽ (፩) ተሰርዞ በሚከተለዉ አዲስ ንዑስ አንቀጽ (፩) ተተክቷል፤

"፩/ የልደት ምዝገባ ቦታ ባስመዝጋቢዉ መደበኛ መኖሪያ ቦታ አቅራቢያ ወይም የጉዲፈቻ ልጅነት ወይም አባትነትን በፍርድ ቤት ማሳወቅ ከሆነ የጉዲፈቻ ስምምነቱን ባጸደቀው ወይም ውሳኔውን በሰጠው ፍርድ ቤት አቅራቢያ ወይም በመደበኛ መኖሪያ ቦታቸው አቅራቢያ የሚገኝ አስተዳደር ጽሕፈት ቤት ይሆናል፤"

፱/ የአዋጁ አንቀጽ ፳፱ ተሰርዞ በሚከተለዉ አዲስ አንቀጽ ፳፱ ተተክቷል፤

5/ Sub-article (1) of Article 11 of the Proclamation is deleted and replaced by the following new sub-article (1):

"1/ Any register of civil status shall be prepared in the form of a bound book or with appropriate technological system."

6/ Article 23 of the Proclamation is deleted and replaced by the following new Article 23:

**23. Signature**

A person required to confirm the particulars entered in register of civil status in accordance with article 22 of this Proclamation:

1/ shall affix a signature in writing,

2/ shall affix his finger print, if he cannot sign in written form

3/ if he is not able to sign in written form or affix finger print, the civil status officer shall sign before a witness by stating reasons.

7/ Sub-articles (2) of Article 24 of the Proclamation is deleted and replaced by the following new sub-article (2):

"2/ The child's parent's full name date and place of birth, principal residence, marital status, citizenship, religion, ethnic origin and, their signatures or signature of the delegated parent.

8/ Sub-article (1) of Article 28 of the Proclamation is deleted and replaced by the following new sub-article (1):

"1/ The place of registration of birth of a child shall be the nearest administrative office to the principal residence of the declarants or the court approved or decided in the case of adoption and judicial declaration of paternity or their principal residence;"

9/ Article 29 of the Proclamation is deleted and replaced by the following new Article 29:

www.chilot.me

"፳፱. <u>ልደትን ስለማሳወቅ</u>

፩/ ልደቱ የተከሰተዉ በጤና ተቋም ዉስጥ የሆነ እንደሆነ ተቋሙ አግባብ ያላቸዉን መረጃዎች የያዘ ማሳወቂያ ቅጽ ወዲያዉኑ ሞልቶ ልደቱን ለማስመዝገብ ግዴታ ላለበት ሰዉ መስጠት አለበት፡፡

፪/ ልደቱ የተከሰተዉ ከጤና ተቋም ዉጭ የሆነ እንደሆነ በዝቅተኛዉ አስተዳደር እርከን ላይ ያለዉ የጤና መዋቅር ወይም የጤና ባለሙያ አግባብ ያላቸዉን መረጃዎች የያዘ ማሳወቂያ ቅጽ ወዲያዉኑ ሞልቶ ልደቱ የተከሰተበት ቦታ ለሚገኘው የምዝገባ ጽሕፈት ቤት ማሳወቅ አለበት፡፡"

፲/ የአዋጁ አንቀጽ ፴፮ ተሰርዞ በሚከተለዉ አዲስ አንቀጽ ፴፮ ተተክቷል፤

"፴፮. <u>የፍቺ ምዝገባ ቦታ</u>

የፍቺ ምዝገባ ቦታ ፍቺዉ የተፈጸመበት ፍርድ ቤት አቅራቢያ በሚገኝ አስተዳደር ጽሕፈት ቤት ወይም በተፋቺዎች መደበኛ መኖሪያ ቦታ በሚገኝ አስተዳደር ጽሕፈት ቤት ይሆናል፡፡"

፲፩/ የአዋጁ አንቀጽ ፵፩ ንዑስ አንቀጽ (፫) ተሰርዞ በአዲስ ንዑስ አንቀፅ (፫) ተተክቷል እና አዲስ ንዑስ አንቀፅ (፬) ተጨምሯል፤

"፫/ ሞቱ የተከሰተዉ በጤና ተቋም ዉስጥ ከሆነ ወይም አስክሬን ለምርመራ ወደ ጤና ተቋሙ የመጣ እንደሆነ ተቋሙ የሟችን ስም፣ ጾታ እና የትዉልድ ቀን፣ የሞተበትን ቀን፣ ቦታ እና የሞቱን ምክንያት እና የመሳሰሉ መረጃዎችን የያዘ የሞት ማሳወቂያ ቅጽ ወዲያዉኑ ሞልቶ ሞቱን የማስመዝገብ ግዴታ ላለበት ሰዉ መስጠት አለበት፡፡

፬/ ሞቱ የተከሰተዉ ከጤና ተቋም ዉጭ የሆነ እንደሆነ በዝቅተኛዉ አስተዳደር እርከን ላይ ያለዉ የጤና መዋቅር ወይም የጤና ባለሙያ አግባብ ያላቸዉን መረጃዎች የያዘ ማሳወቂያ ቅጽ ወዲያዉኑ ሞልቶ

"29. <u>Notification of Birth</u>

1/ Where birth takes place in a health institution, the institution shall forthwith prepare a notification paper containing the relevant particulars and give such notification paper to the person having the duty to declare the birth.

2/ Where birth takes place out of a health institution, the health institution or the health professional found at the lowest level of administrative hierarchy shall forthwith prepare a notification paper containing the relevant particulars and give such notification paper to the nearest administrative office found at birth place."

10/ Article 36 of the Proclamation is deleted and replaced by the following new Article 36:

36. <u>Place of Registration of Divorce</u>

The place of registration of divorce shall be the nearest administrative office to the court where the divorce took place or in the administrative office where principal residence of divorcing partners is located.

11/ Sub-article (3) of Article 41 of the Proclamation is deleted and replaced by the following new sub-articles (3) and add a new sub-article (4):

"3/ Where a death occurs in a health institution or a corpse is brought to it for examination, the institution shall forthwith prepare a notification paper of death containing the name, sex and date of birth of the deceased, the date, place and cause of death and other related information and give the notification paper to the person having the responsibility of declaring the death.

4/ Where death occurs out of a health institution, the health institution or health professional found at the lowest level of administrative hierarchy shall forthwith prepare a notification paper containing the relevant particulars and give such notification paper to the nearest administrative

www.chilot.me

ሞቱ የተከሰተበት ቦታ ለሚገኘው አስተዳደር ጽሕፈት ቤት ማሳወቅ አለበት፡፡"

፲፪/ የአዋጁ አንቀጽ ፵፭ ንዑስ አንቀፆች (፩) እና (፫) ተሰርዘው በሚከተሉት አዲስ ንዑስ አንቀፆች (፩) እና (፫) ተተክተው ከንዑስ አንቀጽ (፫) ቀጥሎ አዲስ ንዑስ አንቀጽ (፬) ተጨምሮ ነባሮቹ ንዑስ አንቀፆች (፬)፣ (፭)፣ (፮) እና (፯) እንደቅደም ተከተላቸው (፭)፣ (፮)፣ (፯) እና (፰) ሆነው ተሸጋሽገዋል፤

"፩/ የክብር መዝገብ ሹሙ የወሳኝ ኩነት ምዝገባ በተጠናቀቀ በ፵፭ ቀናት ውስጥ የምዝገባ ቅጹን ሦስት ቅጂዎች አግባብ ላለው የክልሉ አካል መላክ አለበት::

፫/ የኢትዮጵያ ሚሲዮን የወሳኝ ኩነት ምዝገባ ባጠናቀቀ በ፴ ቀናት ውስጥ የምዝገባ ቅጹን ሦስት ቅጂዎች ለውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር መላክ አለበት፡፡

፬/ የብሔራዊ መረጃ እና ደህንነት አገልግሎት የወሳኝ ኩነት ምዝገባ ባጠናቀቀ በ፴ ቀናት ውስጥ የምዝገባ ቅጹን ሁለት ቅጂዎች አግባብ ላለው የፌደራል አካል መላክ አለበት::"

፲፫/ የአዋጁ አንቀጽ ፵፮ ንዑስ አንቀፆች (፩) እና (፪) ተሰርዘው በሚከተሉት አዲስ ንዑስ አንቀፆች (፩)፣ (፪) እና (፫) ተተክተዋል፤

"፩/ የወሳኝ ኩነት ምዝገባ ምስክር ወረቀት በክብር መዝገብ ላይ ከሰፈሩት መረጃዎች ወሳኝ የሆኑትን የተመረጡትን መያዝ አለበት፡፡

፪/ የወሳኝ ኩነት ምዝገባ ምስክር ወረቀት በሚመለከተዉ ክልል የሥራ ቋንቋ እና በአማርኛ የሚዘጋጅ ሆኖ እንደ አግባብነቱ እንግሊዘኛ ቋንቋን ሊጨምር ይችላል፡፡

፫/ የኢትዮጵያ ሚሲዮን፣ የብሔራዊ መረጃ እና ደህንነት አገልግሎት፣ የኢትዮጵያ መርከቦች እና የሀገር መከላከያ ሚኒስቴር የወሳኝ ኩነት ምዝገባ ምስክር ወረቀትን በአማርኛ እና በእንግሊዘኛ

office found at death place."

12/ Sub-articles (1) and (3) of Article 45 of the Proclamation are deleted and replaced by the following new sub-articles (1) and (3) and after sub-article (3) new sub-article (4) is added and existing sub-articles (4), (5), (6) and (7) are re-numbered as sub-articles (5), (6),(7) and (8), respectively:

"1/ The officer of civil status shall send three copies of the registration form to the appropriate regional organ within 45 days following the date of completion of the registration of a vital event.

3/ An Ethiopian Mission shall send three copies of the registration form to the Ministry of Foreign Affairs within 30 days following the date of completion of the registration of a vital event."

4/ The National Intelligence and Security service shall send two copies of the registration form to the appropriate federal organ within 30 days following the date of completion of the registration of a vital event."

13/ Sub-articles (1) and (2) of Article 46 of the Proclamation are deleted and replaced by the following new sub-articles (1) (2) and (3):

"1/ A certificate of registration of vital events shall contain the selected particulars entered in the register of civil status.

2/ Certificate of registration of vital events shall be prepared in the working language of the concerned region and in Amharic, and as necessary may add English language.

3/ The Ethiopian Mission, the National Intelligence and Security service, an Ethiopian ship and the Ministry of National Defense shall prepare the certificate in Amharic and English languages."

www.chilot.me

ቋንቋዎች ያዘጋጃሉ፡፡"

፲፬/ የአዋጁ አንቀጽ ፵፯ ንዑስ አንቀጽ (፭) ተሰርዞ በሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀጽ (፭) ተተክቷል፤

"፭/ ሌሎች የወሳኝ ኩነትን እንዲመዘቡ ሥልጣን የተሰጣቸው አካላት የወሳኝ ኩነት ምዝገባ ምስክር ወረቀት የሚሰጡት በሚኒስትሮች ምክር ቤት በሚያወጣው ደንብ መሰረት የአገልግሎት ክፍያ በማስከፈል ይሆናል፤ ክልሎች የራሳቸውን የአገልግሎት ክፍያ ደንብ ሊያወጡ ይችላሉ፡፡"

፲፭/ ከአዋጁ አንቀጽ ፶፪ ንኡስ አንቀጽ (፪) ቀጥሎ የሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀጽ (፫) ተጨምሯል፤

"፫/ የቀድሞ ምዝገባ እንዲታረም ወይም አዲስ ምዝገበ እንዲከናወን በፍርድ ቤት ከተወሰነ ውሳኔው ከተሰጠበት ቀን ጀምሮ በ፴ ቀን ውስጥ ምዝገባው በውሳኔው መሰረት መከናወን አለበት፡፡"

፲፮/ የአዋጁ አንቀጽ ፷፯ ንዑስ አንቀጽ (፪) እና (፬) ተሰርዘው በሚከተሉት አዲስ ንዑስ አንቀጾች (፪) እና (፬) ተተክተዋል፤

"፪/ በሥራ ላይ በነበሩ ሕጎች ወይም ልማዳዊ አሰራሮች መሰረት የተከናወኑ የወሳኝ ኩነት ምዝገባዎችና የተሰጡ ምስክር ወረቀቶች ጸንተዉ የሚቆዩ ሆኖ፣ ምስክር ወረቀት ከጠፋ ወይም ከተበላሸ ወይም ከአገልግሎት ዉጭ ከሆነ ከቀድሞ ክብር መዝገብ ላይ ተገልብጦ ምትክ ምስክር ወረቀት ይሰጣል፡፡

፬/ በሥራ ላይ በነበሩ ሕጎች ወይም ልማዳዊ አሰራሮች መሰረት ሳይመዘገብ የቆየ ወሳኝ ኩነት ከደጋፊ ማስረጃ ጋር ተያይዞ የቀረበ እንደሆነ ተመዝግቦ የወሳኝ ኩነት ምስክር ወረቀት ይሰጣል፡፡"

፲፯/ ከአዋጁ አንቀጽ ፷፯ ቀጥሎ አዲስ አንቀጽ ፷፰ ተጨምሮ ነባሮቹ አንቀጾች ፷፰፣ ፷፱ እና ፸ እንደቅደም ተከተላቸው አንቀጽ ፷፱ ፣፸ እና ፸፩ ሆነው ተሸጋሽገዋል፤

14/ Sub-article (5) of Article 47 of the Proclamation is deleted and replaced by the following new sub-article (5):

"5/ Other bodies authorized to conduct registration of vital events shall issue a certificate of registration of vital events upon payment of service fee prescribed by regulation to be issued by council of Ministries; and Regional States may issue their own service fee laws."

15/ The following new sub-article (2) is added after sub-article (3) of Article 52 of the Proclamation:

"3/ Where competent court decides the correction of previous record or the drawing up of a new record, the registration shall be effected in accordance with the decision within 30 days following the date of the decision."

16/ Sub-articles (2) and (4) of Article 67 of the Proclamation are deleted and replaced by the following new sub-articles (2) and (4):

"2/ Vital events registered and certificates issued on the basis of the existing laws or customary practices shall remain valid; but if a certificate is lost, damaged or become out of use, a substitute certificate shall be issued by extracting copies from the old register.

4/ A vital event not registered on the basis of the existing laws or customary practices shall be registered and a certificate shall be issued, if it is accompanied by supporting evidence."

17/ The following new Article 68 is added after Article 67 of the Proclamation and the existing Articles 68,69 and 70 are re-numbered as Article 69,70 and 71, respectively:

www.chilot.me

"፷፰. <u>አገልግሎት ስለማግኘት</u>

የወሳኝ ኩነትን ሥልጣን ካለው አካል ዘንድ ቀርቦ አስመዝግቦ የምዝገባ ምስክር ወረቀት የወሰደ ማንኛውም ሰው የክብር መዝገቡ ቅጽ ቅጂ ከሚገኝበት ማንኛውም የመዝጋቢ አካል አገልግሎት የማግኘት መብት ይኖረዋል፡፡"

፫. <u>አዋጁ የሚጸናበት ጊዜ</u>

ይህ አዋጅ በፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የጸና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ ነሐሴ ፩ ቀን ፪ሺ፱ ዓ.ም**

**ሙላቱ ተሾመ (ዶ/ር)**
**የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት**



**"68.** <u>**Receiving Service**</u>

Any person, who registered a vital event under authorized registration office and obtained certificate of registration in according with this Proclamation, shall have the right to get the service from any registration organ where the copies of the record are kept."

**3.** <u>**Effective Date**</u>

This Proclamation shall enter into force on the date of publication in the Federal Negarit Gazette.

**Done at Addis Ababa, on this 7th day of August 2017.**

**MULATU TESHOME (DR.)**
**PRESIDENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**

www.chilot.me

www.chilot.me

www.chilot.me

www.chilot.me

www.chilot.me

www.chilot.me

www.chilot.me